# ከጣራ በላይ!!



ቀለሟ ለጤናሽ እንደምን አለሽ ? እኔ እግዜአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ አባባስ እንዴት ነው ተሻለው? የኔ ነገር እሱንና እማማን ጎድቶዋል። የሰፈራችን ሰዎች ሌጤናቸው እንዴት አሉ? ጎሬቤቶቻችን ፤ አቶ ተማቹስ ልጃቸው ማረፉን ሰማሁ ! ለወያኔ እጅ አልሰጥም ብሎ አጋዚን አጋድሞ ክንዱን የተንተራሰው አሉ : እሱ አሁን ለቅሶም አያስፈልገውም : ማልቀስ ለኔ የፈረንጅ ባሪያ ልሆን ተሰው አገር በግዞት ላለሁት!!

ያለሁበት አገር ወረቀት ጣፍልኝተብሎ የሚለመን የለም። በመከራ አንዱን አግንቼ ድብዳቤ እንዲጥፍልኝ ለምኜው ገና ቀለሟ ብዬ ስጀምር የጀመረ ድዱን ይገለፍጣል እንዲያው ጤናም ያለው አይመስልም : አማርኛም ጠንቅቆ አያውቅም : ምን ማለት ነው እያለ አሥሬ ይጠይቀኛል : የልጆቻችን ትምህርት ከዛ ከቅኔ ትምህርትቤት የጀመረ ቢሆን ኖሮ የት በደረስን ነበር ፈረንጅም ጉድ አያደርገንም ነበር ።

ሚካኤል ነው ስለው ይስቃል : መቼ ነው መገልፈጥ የምታቆመው ስለው ይስቃል : ታዲያ ምን አልኩ መሰለሽየተፈጥሮ እውቀት የሌለው ዲግሪና ሙት ሰው አንድ ነው አልኩ: አስፈግጎታል ጣፍም ስለው ይጥፋል አልገባውም መሰለኝ : ዲግሪ የሚሏትን ቃል ሲሰማ:ያው ነጮቹ በሱ አይደል የካኑት : ያገሩን ሳያውቅ በነሱ ትምሕርት በመዝለቁ በቁመናው እንደሞተ አሰብኩት እጅጉን ከልቤ አዘንኩለት!! ገንዘብ አፍስሰን ያስተማርናቸው እንደሱ የሞቱ ስንት ናቸው ብዩ በሃሳብ ነጎድኩ። ያገርኛውን ያልተማሩ ወይም ባሕሉን ጠንቅቀው የማያውቁ እንዴት ብለው አገሬውን ይመሩታል? እንዴትስ አገር ሊረኪቡ ይችላሉ !! የኛ የሆነውን ሁሉ አውልቀው ጥለውታል : ቆዳቸው ጠቆረ እንጂ ወደ ነጮቹ አድልተዋል : ነጩ ደግሞ አልቀበልህ ብሎት እንዲያው ሲባዝኑ ዘረኝነት እያሉ ሲያለቅሱ እሰማለሁ።

በቀደም ወደ ልብስ ማጠቢያ ቤት አለፍ ስል ያገኘኋት አንዲት ያገሬ ሰው እዚህ ሰፈር ነው ይምትኖሩት ብላ ጠይቃ ካወጋችኝ በኋላ የልጅዋን ልደት ጋብዛኝ ሄድኩ : ጉድ ጉድ የልጁ መዓት : ወልደው ወልደው አማርኛን : የመላዕክት ቋንቋን አላስተማሯቸውም፣ ስምህ ማነው ዝም : ስንት ዓመትህ ነው? በትርጁማን ሆነ መልልሱ : ታዲያ ልጆቻችሁን

መሃይም አደረጋችኋቸው ስል እነሱም ከጣራ በላይ ሳቁ : እኔ ግን ከልቤ አዘንኩ አገር አልባ ሊያደርጓቸው ነው እንዴ አልኩ : አገራችን የመጣ ቻይናና : ሕንድ ከነልጁ ጭምር አቀላጥፎ አማርኛ ቋንቋን እየተናገረ እንሱ ልጆቻቸውን ነፍጉዋቸው።

እንደ ጅግኖቹ አባቶቻችን ሳንታኮስ : አገር ሳንጠብቅ እንደዋዛ አገራችንን አጨብጭበን ማስረከባችን ይሆን ብዬ አሰብኩ!! ተዛው ከልደቱ ቤት ተጠራርተው የመጡትን ያገሬን ሰዎች ሳደምጥ እንዳው አማርኛው ውስጥ የፈረንጅ ቋንቋ ሰንቅረው ሰንቅረው ልረዳቸው ሳልችል ቀርቼ ከጨዋታው ውጭ ሆኜ ዋልኩ : ልደቱም መከበር ሲጀመር የሻማ መዓት ደርድረው" ሃፒ" የምትለውን ብቻ አስታውሳለሁ እንጂ በፈረንጅኛ አስነኩት : ምን አላችሁ ስላቸው መልካም ልደት ነው ያልነው አሉኝ!! እኔን የቆጨኝ በአማርኛ የዘመሩት የፈረንጁን "ሃፒ" ካስቀደሙ በኋላ ነው : በአማርኛ ቋንቋ መልካም ልደት አለመጀመሩ ቅር አሰኝቶኛል : እና ይሄ ወዴት ይዟቸው እንዴሚሄዱ ጌታ ይወቀው።

አባቴ በደርግ ዘመን አራትኪሎ ካለው የአርበኞች ቢሮ ቢጤዎቻቸውን ለመጠየቅ ብቅ ብለው አንድ ነገር ተመልክተው ሲቆጡ ዋሉ : እኔን ና አሉኝና ተመልከት አሉኝ ማዶ ትልቁ ሰዓት ወዳለበት ወደ ፓርላማ በጣታቸው እያመለከቱ ፣ ምንድ ነው ስላቸው ? **ተመልከት የኮሚኒስት ባንዲራ ከኢትዮጵ ባንዲራ ከፍ ብሎ ተሰቅሎዋል ብለው እንዳስተውል አደረጉኝ እኔም አብሬ አዘንኩ፣ የዛሬውስ ትውልድ ቋንቋውን እስኪያጣ ዲዳ ሲሆን ምንኛ ያበግን ይሆን!! እኔ እንኳን ተገንዝቤዋለሁ ዳዊት ያልደገምኩት : ቅኔ ያልቃኘሁት ማህይሙ።**

**አበው ያስተማሩን ከየት እንደመጣን ከላወቅን ወዴት ልንሄድ እንደምንችል አናውቅም ብለው አበክረው ነግረውናል። የራስን አጥብቆ መያዝ ያስከብራል : ያኮራል።**

ካገሬ ከወጣሁ ይኸው ጥቅምት 19 የገብርኤል ዕለት አንድ አመት ሆነኝ : አቤት ጊዜው መንጎዱ : አንቺዬ በጣም ናፈኩሽማ : ወቸው ጉድ ናፍቆት እንደ እብድ ያደርጋል ምነውሳ እንዲህ ብለሽ ግጥም አልገጠምሽልኝ ?

"አለቅሳለሁ ባይኔ አብሳለሁ በጄ፣

እንደሰማይ ኮከብ እርቆ ወዳጄ።"

እንዲያው አልናፈኩሽም መሰለኝ።

በተሰደድኩበት አገር የወፍ ዝማሬ የለ : የከብት ድምጽ በቀየው አይሰማ : ወይ ነዶ ያገሬ በሬ ግጦ ግጦ ሲያገሳ ደስ ሲል : ሰፋሩን ይደባልቀዋል : ያለሁበት አገር ግን ከዋክብት ወደሰማይ ቀና ቢሉ አይታይ እንዲያው ኮረንቲ ብርሃን ብቻ ። ድንቄም የፈረንጅ አገር በር እየዘጉ በቀዳዳ እያዩ ነው በሩን የሚከፍቱት እንግዳ ሲመጣ። ያገሬ ሰዎች ጭምር በራቸውን ከርችም አድርገው ዘግተው መቀመጥ ለምደዋል፣ እኔ ግን ምሽግ ውስጥ

አልገባሁም አሻፈረኝ በማለት ወለል አድርጌ እንደከፈትኩት ያለሁት ወደፊት እኔስ እለወጥ ይሆን ብዬ አስባለሁ ፡ በሩ ቢከፈትም ዝር የሚል ሰው እንኳ የለም።

ያገሬ ሰው ጠያፍ ነገር በደጁ የተጠላ ልክ እንደ እግዚአብሄር ደግ ህዝብ ነው ። ፈረንጅ መሠሪነቱን ነው የተረዳሁት ፡ በቀደም ወደከተማ ወጣ ስል አንድ ተስፋዬን የሚመስል በስቋላ ወጣት ቆሻሻ ሲለቅምና መንገድ ሲያጸዳ አገኘሁት ፡ በከዘራዩ ጎሸም አድርጌ ከየት ነህ ስለው? ከኢትዮጳያ አለኝ እንዲያው ፊቴ ልውጥ ብሎ አመድ ለበሰ ፡ ምን ነክቶህ ነው ስለው ምንም አለኝ ፡ ለምን ይህን ሥራ ትሰራለህ ? ገንዘብ ከቸገረህ ልስጥህ ብዬው ኪሴ ስገባ እንባውን አፈሰሰው ፡ ለካስ ገራገር ኖሮዋል አልቅሶ አስለቀሰኝ ፡ ልብ በይ የፈረንጅ መሰሪነቱን!! አንድ ግጥም ትዝ አለኝና እንዲህ አልኩ!!

”ካገሩ የወጣ ካገሩ እስኪመለስ፣

ቢጭኑት አህያ ቢጋልቡት ፈረስ”

እንባዬን በነጠላዩ አብሼ ፡ ሳነጋግረው ለካስ ፈረንጅ ስራ አልሰጥም ብሎት ኮሌጅ የበጠሰ ወጣት ኖሮዋል ! ንዴት ገባኝና ኪሴ ያለኝን ገንዘብ ጎልጉዬ ና ወላዲት አምላክን መሳፈሪያህን እከፍላለሁ ቃለ ለምድር ለሰማይ ነው እንሳፈር ባቲ እንገባለን ፡ ኢትዮጵያ አገራችን ናት ጣሊያንን ደምስሰናል ወያኔን እንወቅጠዋልን እንግባ ስልው ግዜ አሁንም አንባውን አፈሰሰው !! ሰው ለካስ እንደጉድ ይመለከተን ኖሮዋል ። እኔም ሳላቅራራ አልቀረሁም!! ፈረንጅ ሸከኛ ነው ።

አይ አንቺ ኢትይጵያ፣ ልጆችችሽን ለግዞት ሰደድሽ

በሕንድ በፓኪስታን፣ ተደፈርሽ

መጤ ቱርክ፣ፈሰሰብሽ፣

ላልተወለዱሽ ፣ መገበርሽ

ለሞቱልሽ ለጀግኖቹ ልጆች ፣በር ዘግተሽ

ልጆችሽን ባገራቸው፣ባሪያ አድርገሽ

ነጻነትሽን በድፍረት፣ የወሰደብሽ

ጉግማጉንግ ወያኔ፣ሲያዋርድሽ

ምነው አልተቆጣሽ፣አልተነሳሽ

እምቢ አሻፈረኝ፣ ለምን አላልሽ

መርዶ ላርዳሽ፣ስለተሰደዱ ልጆችሽ

ያረብ አሽከር፣ወሲብ ማርኪያ ሆኑልሽ

ግማሾቹ ባህር በላቸው፣በመንገድ አለቁልሽ።

ሁሌ አንቺን በመጥራት ፣አቅሜ ተለዘ

ወያኔ ጠላት ነው ፣ታሪክ የደለዘ።

በይ እርምሽን አውጪ ኢትዮጵያ!!

ቀለም ፖለቲከኛ ሆንክ ብለሽ እንዳታስቢ ብቻ ያ ኮሌጅ ያጠናቀቀው ልጅ አንዳንድ ነገር ይዞ ይመጣና ሹክ ይላል : አንድ ትንሽ ተሌቪዥን የመሰለች ነገር ያመጣና ወሬ ያቀብለኛል።

ከሰሞኑ ፐሮፌሰር መስፍን አበሻ እያሉ ጽፈዋል ብሎ ሲቆጣ ነበር : እንዴ ፈረንጅ ነን ወይ ስለው ? ዘርዝሮ አስረዳኝ፣ ሊቅ ነው አበሻ የሚለው ቃል የውርደት ስም ነው ያአለቃ ታዬን መጥሃፍ ማንበብ ይረዳል ብሎ አስተምሮኛል፣ እሳቸውስ ቢቀርባቸውስ ኢትዮጵያዊ ቢሉስ፣ ቢያርሙት ምን አለበት!! እንዲያው የሚያስተምሩን ነገር ካለ እስቲ በዚህ ላይ ብቅ ይበሉ!!

በቀደም ጉድ ሆንኩልሽ ብርድ መግቢያው ስለሆነ ካገሬ ያመጣኋትን ነጠላ አጣፍቼ እየተሽቀነደርኩ ብቅ ስል የሰፈሩ ነጫጭባ ሕጻንት ሁሉ ልክ እንደ ጉንዳን ወረሩኝ መስኮት እየከፈቱ ነጮቹ ዓይኔን አወጡት ፣ እንዴት ጠብድለዋል ግማሾቹ አሳማ ምስጋና ይንሳው።

ትንሽ ቆይቶ አንቡላንስ የመሰለ መኪና ብቅ አለች : በኋላ ስሰማ ስልክ ደውለው ኖረዋል : እየተቆጣ ወደኔ ሲቀርብ ወጊድ ዘራፍ ብዬ ጎሽም አደረኩት መሰለኝ በዱላዬ : ከዚያ በኋላ የሆንኩትን አላውቅም : ከእንቅልፌ ስነቃ በዛብህን ከጎኔ ቁጭ ብሎ አገኘሁት : ነካስ መተውኝ ኖሮ ነፍሴን አላውቅም ነበር። በዛብህ እኔ ካለሁበት መንደር ይኖር ስለነበር "stop" እያሉኩ ስሮጥ እኔንም አገቱኝ አለኝ : ለዚህ ነው ኩምትር ብሎ ከእንቅልፌ ስነቃ ከእስር ቤት ከጎኔ ቁጭ ብሎ ያገኘሁት : እስር ቤት ይሉታል እንጂ ቪላ ቤት ነው።

ያኮሌጅ በጥሶ ጎዳና ፈረንጅ የሚያስጠርገው ልጅ እቤቴን አሳይቼው ኖሮ ሊጠይቀኝ ሲመጣ አንዲት ጋዜጣ ይዞ መጥቶ ፎቶህ በጋዜጣ ላይ ወጥቶዋል አለኝ ፣ አንቺዬ እንዴት አምራላሁ ሳላውቀው እንዴት ፎቶ እንዳነሱኝ ግርም ብሎኛል። እስቲ አንብበው ምን ይላል ስለው ? የጥቃት ሙከራ በፖሊስ ላይ ያደረገው የባቲ ሰው ታግቶ ተፈታ ካለ በኋላ ዱላን እንደሻቦላ ተጠቅሞ ጥቃት በፖሊስ ላይ በመሰንዘር ሕግ ተላልፏል በማለት አንበለበለው : ጎሬቤቴ ያን ጋዘጣ ቢያነበው ጥሩ ነው ማስፈራሪያ ይሆናል : ሳያነባት የቀረ አይመስልም ዓይኑን ሰሞኑን ያጉረጠርጣል : እኔም ከዘራዬን አለያት ከኔ ጋር።

ካልደከመሽ እኔ ምን ቸገርኝ በቀደም ዶክተር ጋ ሄጄ መነጥር ያስፈልግሃል አለ : አንድ ኢትዮጵያዊ ትሩጅማን ገንዘብ የለኝም ስለው መንግሥት ይከፍልልሃል አለኝ።

ስለምን ትከፍልልኛለህ ያገሬ መንግሥት ያልከፈለልኝን : መንደሬን አፍርሶ ያባረረኝ : ሕጻናት ልጆቼን ከትምህርት ቤት የበተነ፣ማዳበሪያ ክፈል እያለ ጎሮሮዩን እያነቀኝ አንተ ስለምን ትከፍልልኛለህ ስለው ፈገግ ብሎ ሳቀ።

ጉድ ነው የሰው አገር መንግሥት ላገሩ ቀርቶ ለውጭ ሰው ይጠራል አልኩ!! ብቻም ጥርጣሬ ገብቶኛል ኩላሊት ይወስዳሉ የሚባል ወሬ ስላለ ሰውነቴ ራደ አይዞህ ብሎኛል ትርጁማኑ። አልኮተልከም አልኩት እሱንም አይዞህ ብሎኛል። ታዲያ ምን ፈልጎ ነው? አረ ጉድ ነው ቀለሟ ወንዱ ወንዱን ይወዳል አሉ እዚህ ያለሁበት አገር ፣ ፍናፍንት ሞልቷል።

በስም ዓብ ብልጭ አለብኝና ዋ ብዩ ነግሬዋለሁ ፣ ሌላ ነገር ፈልገህ ከሆነ አይማረኝ አልምርህም አልኩት ፣ ትርጁማኑም የነገር ቋት ነው ያልኩትን ሳያስቀር ይተንፍሳል። ፈረንጁ በመገረም አየኝና ተሰነባበተኝ።

አዲስ መጫሚያ ለኔ አዲስ ነገር ሆኖ ሸፈፍ ሸፈፍ ያደርገኛል : በቀደም አንዱን ፈረንጅ ጉድ አደረኩት : ስንሻፈፍ አዳልጦኝ ከላዩ ላይ ተከመርኩበት እየተበሳጨ የሚለው ሳይገባኝ ሄደ ግን እንደተናደደብኝ ይገባኛል : እንዲያው እንደ አዲስ የተፈጠረ ሕጻን ልጅ መሰልኩ : በእግሬ እንደዛ እንዳልሮጥኩበት ።

ብርዱ አይቻልም እንጂ እኔስ በእግሬ አለጫማ መሄዱን እመርጣለሁ : እንዲያው በጥንቃቄ ነው የምረግጠው : ፈረንጅ ቡዳ ነው አውቆብኝ መሰለኝ በየሄድኩበት ትኩር ብሎ ይመለከተኛል : አይ መንሻፈፍ !!

ሲከፋኝ ከፍ አድርጌ ያዜምኩ ከሆነ : ከጣራ በላይ ጮሀሃል ተብዩ በአስተርጓሚ ማስጠንቀቂያ ተነግሮኛል። ድሮ የአቶ በሪሁን አዛለ ልጅ ትምሕርቱን ውጭ አጠናቆ ከመጣ በኋላ የመናገር ፣ የመጻፍ ፣ የመሰብሰብ የመሳሰሉት መብቶች በውጭው ዓለም አለ ብሎ ሲሰብክ ነበር፣ ታዲያ እኔ ከፍ አድርጌ ባቅራራሁ ስለምን ከጣራ በላይ ተናግረሃል ተብዩ እወነጀላለሁ፣ ድንቄም ዲሞክራሲ ጮኸው የማይተነፍሱበት : የፈለኩትን ለብሼ ብወጣ አይኑን አያጉረጠረጠ የሚሄድ ሕዝብ ጉድ ነው!! ያ የባቲ ምኩራብ ይምጣብኝ እንደ ልቤ ዘራፍ ብዩ የማቅራራበት : ብፈልግ የምዘፍንበት ፣ ቢያስፈልገኝ ድምጼን ከፍ አድርጌ ወግ የማወጋበት ነው : አይ የሰው አገር ደግሞ አይኩራሩበት።

ያገሬ ነዳይ በገነት ቁጭ ብሎ ነው ምጽዋት የሚለምነው አልኩ : ያገሬን ውበት አድንቄ እኔ ወያኔን መዥገሩን ከመነገልን የገነቱ ኑሮዋችን ይቀጥላል።

"ዋልዳና ደላንታ ፣ ሁሉም አገር ነው

እንዴት የጁን ጥሎ ይቧዝናል ሰው"።

መይሳው ከምድረ ስዊድን!!

2013-11-09